# ‘አዲስ ነገር’ ተዘጋች አሉ

በአህመድ አባጊሣ

‹አዲስ ነገር›ን የማውቃት ከመስከረም ወር 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ነበረ፡፡ ዘወትር ቅዳሜ ይህችን ጋዜጣ ገዝቼ እንዳነብ የሚያደርጉኝም በርካታ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ መጀመሪያ ላይ ስጀምር በወቅቱ የነበሩት አብዛኞቹ ጋዜጦች የፊትም ሆነ የውስጥ ገፆቻቸው ብዙም የማይስቡ ሲሆኑ፤ ከውጪ በጣም የሚጮሁ፤ የሕዝብን ስሜት አጉል ለማነሳሳት ሲባል እንደሚፃፉ የሚያስታውቁ እና ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ ላይ ያለው ባዶ ጩኸት መሆኑን የሚያረጋግጡ፤ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ እጥረትና የሚዛናዊነት ችግር የሚስተዋልባቸው ሆነው አገኛቸው ነበረ፡፡ ‹አዲስ ነገር› ግን በተለይም ከአዘጋጆቹ አንዱ የነበረው አቢይ ተ/ማርያም ቀደም ሲልም በምርጫ 97 ‹መዝናኛ› የምትል ጋዜጣ ይዞ ተጽዕኖ መፍጠር የቻለ ስለነበረ በዚያ ምክንያት ሰከን ያለ፤ ዝርዝር ትንታኔም የሚሰጥ ነገር አገኛለሁ ብዬ ተማምኜ ማንበብ ጀመርኩ፡፡

‹አዲስ ነገር› በእርግጥም ልክ እንደ ቀድሞው ‹መዝናኛ› ትንታኔን እንዲያውም ፈጽሞ ባልጠበቅኩት እና ባልገመትኩት መጠን ማቅረብ ብቻም ሳይሆን፤ ቀደም ሲል በ ‹መዝናኛ› ጋዜጣ ላይ ያልነበሩ አዳዲስ አምዶችን (ከፓርላማን እና የሳምንቱ ጉዳዮችን ልብ ይሏል) እና አምደኞችን በመያዝ ብቅ ማለቷ እጅግ አስደሳች ነበረ፡፡ ትንታኔዎቹ አቅጣጫን ጠቋሚ፤ አስተማሪና ምንም እንኳ ብዙውን ግዜ የመንዛዛትና አንዳንዴም ከጭብጡ ወጣ ባሉ የውጭ ምሳሌዎች የተጠቀጠቀና የተሞላ ቢሆንም ለፖሊሲ አውጪዎችና ለፖለቲካ መሪዎች በግብዓትነት ሊጠቅም የሚችል ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ትንታኔዎቹ ነባራዊ ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እውነታዎችን በችኮላና በስሜት ሳይሆን ሰከን ባለ መልኩ ኅብረተሰቡ፤ የፖለቲካ መሪዎች እና ታዛቢዎች ብሎም ዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብ እንዲመለከተው ከፍተኛ አስተዋጾ አድርገዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ‹አዲስ ነገር›ን ገዝቼ እንዳነብ እና ለማንኛውም ለሌላ ጋዜጣ ያላደረግኩትን እና ከዚህም በኋላ እንደማላደርገው እርግጠኛ የምሆንበትን የተለያዩ ፖለቲካዊ እና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የራሴን ሀሳብ መሰንዘርና በጋዜጣው አስተያየቶች መሰንዘር ድረስ ያደረሰኝ የጋዜጣዋ ገለልተኝነት ነበረ፡፡ ‹አዲስ ነገር› እኔ እስከማውቀው ድረስ ለማንኛውም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲ ያልወገነች፤ ሁሉንም በእኩል ለማስተናገድና ፍትሀዊ የሆነ በፓርቲዎች መሀከል ያለ መስተጋብርን እና የሐሳብ ልውውጥን ታበረታታ ነበረ፡፡ ‹አዲስ ነገር› እንደ ቀሪዎቹ የአገራችን ፕሬስ ውጤቶች ተቃዋሚዎችን እና ገዢውን ፓርቲ በሆነ ባልሆነው ከመንቀፍ፤ ወይንም ከማሞገስ ይልቅ ሁለቱም ወገኖች ሊያዩዋቸው የሚገቡ ጭብጦች ላይ በማተኮር፤ በተለይም በፓርቲዎቹ የፖለቲካ ፕሮግራሞች፤ አይዲኦሎጂ እና አደረጃጀት ላይ ያሉ ጥንካሬ እና ድክመቶችን በብቃትና በቋሚነት እየፈተሸችም ፓርቲዎቹ እነዚያን አስተካክለው እንዲሄዱ መጣሯ ልዩ ያደርጋታል፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ግዜ አዘጋጆቹ እንደማንኛውም ሰው ምናልባትም የውጭ ዲፕሎማቶችና የውጭ ጋዜጠኞች የሚሰነዝሯቸውን እና ከተጨባጩ እውነታ ጋራ ብዙም የማይጣጣሙ አስተያየቶችን ተቀብለው የሰነዘሩባቸው ወቅቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ያ ማንንም ፓርቲ ለማዳከም፤ ወይንም ሌላኛውን ለመደገፍ ሳይሆን ‹ይህን መሰሉ ተቃውሞ እና ትችት በዚህ ፓርቲ ላይ ይቀርባል› የሚለውን አንደምታ ለመፍጠር ነበረ፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ‹አዲስ ነገር›ን እንድወዳት ያደረገኝ በአገራችን በዘመነ ሕወሓት ፈጽሞ ያልነበረውን በፕሬሶችም ታይቶ የማይታወቀውን ዓይነት የገለልተኝነት፤ የአመዛዛኝነት እና የጨዋነትን የፖለቲካ ባሕል ለማዳበር ተግታ ትሰራ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ‹አዲስ ነገር›ን አዘውትሮ የሚያነብ ማንኛውም ደምበኛ ራሱን ክፍት ካደረገ የሚጨብጠው ዋንኛ ቁም ነገር ቢኖር የትኛውንም ፓርቲ ጭልጥ ብሎ መደገፍ ጉዳቱ እንደሚበልጥ፤ የሌሎችንም ሐሳብ ማድመጥ የራስንም ለማዳበርና በፖለቲካው መስተጋብር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር የሚረዳ እንደሆነ ነው፡፡ ‹አዲስ ነገር› ከብዙ የግል ጋዜጦች በተለየ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እምብዛም ተቃውሞ የማይቀርብባት ነበረች፡፡ ስሞታ እና ሐሜት ይዘው የቀረቡ የፖለቲካ መሪዎችን እምብዛም አላየንም፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ የንግድ፤ የትምህርትም ሆነ ሌሎች ተቋማት ተቃውሞ ሲያቀርቡም ሆነ ‹ስማችን ጠፋ› ብለው ሲያማርሩ አልተመለከትኩም፡፡

በአራተኛ ደረጃ ‹አዲስ ነገር›ን ልዩ የሚያደርጋት ራሷ ትፈልገው እና በኢትዮጵያችን ውስጥም የበላይ ሆኖ እንዲኖር ትመኘው የነበረውን የፖለቲካ አቀራረብ ሰከን ባለና ከመጣም በኋላ ቢሆን ከተገቢው ትችት ጋራ የተቀበለችው መሆኑ ነው፡፡ እኔ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አደራጅ አባል ስሆን በጋዜጣዋ ላይ ልክ

ፓርቲያችን ከመንግስት እውቅና ለማግኘት ሽር ጉድ በሚልበት ወቅት ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. በ 1ኛ ዓመት ቁጥር 035 ላይ ‹የ‹አንድነት› ሽክምና ተስፋ› በሚል አንድ ፊቸር ተጽፎ ነበረ፡፡ በርግጥ በዚያ ፊቸር ላይ የቀድሞው ቅንጅትን በተመለከተ አንዳንድ የተሳሳቱ አስተያየቶች የተሰነዘሩ ሲሆን በብዙ ክልሎች ድጋፍ እንዳልበረው በማስመሰል ራሷ ‹አዲስ ነገር›ም ‹የምርጫው ውጤት ተዓማኒነት አልነበረውም› የምትለውን እምነትም የሚንድባት የሚያስመስሉ፤ በመረጃ ላይ ያልተመረኮዙ ነገሮች ተጽፈው ነበረ፡፡ ስለ አንድነት ፓርቲም በተለይም ከመኢአድና አገር ውስጥ ከሌለው ግንቦት 7 ፉክክር ይገጥመዋል ተብሎም አስቂኝ ነገር መፃፉ የማይዘነጋ ነበረ፡፡ በወቅቱ እኔም በነዚህ ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመረኮዙ አስተያየቶቼን በ 4 ክፍል በኢ-ሜይል ለአዘጋጆቹ የላኩ ሲሆን የፓርቲያችን መስራች እና ብሔራዊ ም/ቤት አባል አቶ ስለሺ ጠናም በጉዳዩ ላይ ያሰሙት ተቃውሞ ተስተናግዶላቸዋል፡፡ በወቅቱ ‹አዲስ ነገር› ጭልጥ ካለ የብሔርም ሆነ አገር አቀፍ አደረጃጀት ይልቅ በሁለቱ መሀከል አማካይ ስፍራ ማግኘት የተሻለ እንደሆነ ስትጠቁም ይህንን አንቀበልም ካሉት አባላት አንዱ ነበርኩ፡፡ በጋዜጣዋ ላይም የሰላ፤ አንዳንድ ይዘቱም ተገቢ ያልሆነ ትችት ጭምር ጽፌ በኢ-ሜይል መላኬን አስታውሳለሁ፡፡ ዛሬ ላይ ስናየው ፍጹም አብላጫ ቁጥር ያለው የአንድነት ፓርቲ አባል ይህንን እውነታ በመቀበል፤ የተሻለ አደረጃጀት በመፍጠርና፤ የሌሎችንም ሐሳብ አድምጦ በአይዲኦሎጂ ላይ ስር ነቀል ለውጥ ሳይደረግ የተወሰኑ ነገሮች ግን ተጨምረው ቀደም ሲል በተለየ አካሄድ ተደራጅተው ከነበሩ ፓርቲዎች ጋራ ጥምረት ፈጥሮ ‹መድረክ› በተባለው ስብስብ ውስጥ ይገኛል፡፡ ዛሬ ከመሀከላችን 20 እንኳን የማይሞሉ አናሳ ድምጽ ያላቸው አባላት በዚህ ጉዳይ ላይ በድምጽ ብልጫ ስለተሸነፉ እና ለሰሚ እና ለተመልካችም የሚቀፍ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽመው በመባረራቸው ብቻ ይኸው ‹የኛ ሐሳብ የበላይ ካልሆነ አንድነት አይኖርም› የሚሉ እስኪመስል ሊበጠብጡን እየሞከሩና እየከሸፈባቸው ነው፡፡ ስለዚህ አቅጣጫ ጠቋሚዋን ‹አዲስ ነገር›ን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ጋዜጣ ማለት እንዲህ ያልታየውን የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ ለፓርቲያችን የሚጠቅምን ማንኛውንም ነገር አይደለም እንደ ‹አዲስ ነገር› የአገር መኩሪያ ከሆነች ተወዳጅ ጋዜጣ አሁን አሁን ከምናያቸው ቅልጥ ያሉ የተቃዋሚ ደጋፊዎችም ጭምር ልንቀበል ይገባናል፡፡

‹አዲስ ነገር› ‹መድረክ› የተቋቋመበትን መሪ ሐሳብ በዚህ መልኩ አፍልቃለች የሚል ክርክር ሊቀርብ ቢችልም የ ‹መድረክ› ደጋፊ ግን አልነበረችም፡፡ ለአብነት ያህልም በመስከረም 9 ቀን 2002 ዓ.ም በ 2ኛ ዓመት ቁጥር 100ኛ እትሟ ላይ በገጽ 2 እና 3 ላይ ‹የመድረኩ ኤክስፔሪመንት፤ ላረጁ ችግሮች አዲስ ሐሳቦች› በሚል ርዕስ ባወጣችው ፊቸር ላይ ዋና ዋና በሚባሉት አወዛጋቢ ነጥቦች ላይ የራሷን ትችት ሰንዝራለች፡፡ በጥቅል ሐሳቧም የ ‹መድረክ› ማኒፌስቶ መሻሻሎች እንደሚያስፈልጉት እቅጩን ተናግራለች፡፡ ‹መድረክ›ን የሚደግፍ ጋዜጣ ቢሆን ይህንን አያደርግም፡፡ ስለዚህ ‹አዲስ ነገር› ለ ‹መድረኩ› ቀና አመለካከት ቢኖራት እንጂ ደጋፊ ግን ልትባል አትችልም---አትወግንም፡፡

‹አዲስ ነገር› ከእነዚህና በሕዝብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነትን ካስገኟት ጥንካሬዎቿ ባሻገር ጥቂት ድክመቶች እንደነበሩባትም እሙን ነው፡፡ ለምሳሌም ዘወትር ቅዳሜ ዘግይታ የምትወጣበት እና ከሕትመት ግዜ ጋራ የተያያዘው ችግሯ ወደ በኋላ ላይ መጠነኛ መሻሻል ቢያሳይም ለረጅም ግዜ ግን ችግር ሆኖ የቀጠለ ነበረ፡፡ በፊቸሮቿ ላይ የምትዳስሳቸው ርእሶች እጅግ ተመራጭና ተገቢ ቢሆኑም አንዳንድ ግዜ ግን መቋጫ እና መፍትሄ ሳታበጅላቸው መጽሀፍ ሊወጣቸው የሚችሉ ትላልቅ ጉዳዮችን ለአብዛኛው ሕዝብ ትንሽ ግልጽነት በሚጎድላቸው ቀመሮችና የፖለቲካ ሃልዮቶች ለመፈተሽ መሞከሯ ረቂቅ አድርጓት ቆይቷል፡፡ በሌላ በኩል ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ ‹የፖለቲካ ሜሞ›፤ በ ‹የሳምንቱ ጉዳዮች›፤ በ ‹ፓርላማ› እና በመሳሰሉት አምዶቿ ደግሞ አንዳንድ ግዜ በተወሰነው የጎብረተሰቡ ክፍሎች ስለ ገዢው ፓርቲም ሆነ ስለ ተቃዋሚዎች የሚወራውን ልክ እንደ እውነት በመቁጠር በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ሳያስገቡ አዘጋጆቹ እንደራሳቸው አስተያየት ይሁን የጋዜጣው አቋም ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ያንፀባረቁባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል ሚዲያ ወቅታዊ እንደመሆኑ እና መረጃንም በስፋት እና በተከታታይነት ለአንባቢያን ማቅረብ ያለበት ከመሆኑ አንፃር ‹አዲስ ነገር› ምንም እንኳ ከሌሎቹ የግል ጋዜጦች ጋራ ስትተያይ እጅግ የተሻሉ፤ በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ መዋቅር ውስጥ ያሉ ምንጮች ቢኖሯትም አጫጭር ዜና ላይ ግን ደከም ብላ ሰንብታለች፡፡

የሆነው ሆኖ እኔ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እንደማንኛውም የፕሬስ ነፃነት እና ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በአገራችን ተከብሮ እንዲኖር እንደሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የ ‹አዲስ ነገር› አዘጋጆች አገር ለቀው ለመውጣት የተገደዱበት ደረጃ ላይ በመድረሳቸው ከፍተኛ ሐዘን ፈጥሮብኛል፡፡ ‹አዲስ ነገር›ን ማጣት ማለት በአገራችን በተለይም ከተካረረውና በሁለት ጫፍ ተወጥሮ ካለው የጥላቻ የፖለቲካ ባሕል አንፃር ተፈላጊውን መቀራረብና አማካይ ስፍራ ለማግኘት፤ ራስን ለመፈተሽ እና የመከባበር አዲስ አስተሳሰብ ለመፍጠር የሚቻልበትን እድል ማጣት ነው እላለሁ፡፡ ‹አዲስ ነገር›ን ከአገር እንድትወጣ እና ከአንባቢያን እንድትርቅ የመንግስት ስልጣንን እና መዋቅርን

ተጠቅመው ያደረጉ ሰዎች ደግሞ የፕሬስ ነፃነት እንዳያብብ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ለማንም ያልወገነን በምርጫ 97 ወቅትም ቅልጥ ያሉ የተቃዋሚ ደጋፊ ከነበሩ እና የሆነ ያልሆነውን አጋንነው አቅርበው ይኸው ዛሬም አብዛኞቹ ያንኑ ስራ እንዲሰሩ ሲፈቀድላቸው ገለልተኛ የሆነችውን እና የሐሳብ እና የመርህ የበላይነትን ይዛ የቆየችውን፤ ለገዢው ፓርቲም ቢሆን እንደ ጥሩ መስታወት ታገለግል የነበረችን ጋዜጣ መዝጋት ማለት ነው፡፡ ‹አዲስ ነገር› እና አዘጋጀቿን ከፖለቲካው ጫወታ ማስወጣት ማለት የተካረረውን እና በሁለት ጫፍ ያለውን የጥላቻ ፖለቲካ ለማረም እንደ መንግስት የሚጠበቅብኝን ሚና አልጫወትም በማለት በሕዝብ ላይ የሚፈጸም ማን አለብኝነት እና እምቢተኝነት መሆኑ ቅንጣት ታህል አያጠራጥርም፡፡ ‹አዲስ ነገር›ን በስለላ፤ በመንግስት እና በተለያዩ የማሸማቀቂያ መዋቅሮች ተጠቅሞ ከሕትመት ውጭ ማድረግ ማለት በመንግስት ደረጃ የሚፈጸም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ፤ በገዢው ፓርቲ ውስጥ የተንሰራፋውን እና በኢትዮጵያችንም ላይ በግድ ለመጫን እየተሞከረ ያለውን የትምክተኝነት፤ የሙሰኝነት እና የከፋፍለህ ግዛ ጠባብ ብሔርተኝነት እንዲቀጥል በር መክፈት እንደሆነ ሕዝባችን ይገነዘባል፡፡

በ‹አዲስ ነገር› ጋዜጠኞች ላይ የደህንነት ክትትል መደረጉን ቀደም ብዬ ነበረ የሰማሁት፡፡ በወቅቱም በጣም አዝኛለሁ፡፡ ይህ ፕሬስ ለስቅላት እንደተዘጋጀ የሚያመላክት፤ የማንም ደጋፊም ሆነ ተቃዋሚ ሳይሆኑ ገንቢ አስተያየትን በመሰንዘር ተጽዕኖ ለመፍጠርና መረጃንም በሚዛናዊነት ለማቅረብ በሕገ መንግስቱ የተሰጠን መብት ማፈን ማለት ነው፡፡ ‹አዲስ ዘመን› በተባለው የመንግሥታዊ ጋዜጣ ላይም መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም ‹አጀንዳ› በተሰኘው አምድ ላይ ‹ለጥፋት አደግድጎ የተነሣ ጋዜጣ ሁሌ እንደ ሰጋ ሊኖር ግድ ይለዋል› በሚል ርዕስ የመንግስት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚ/ር በሆኑት ከፍተኛ ባለስልጣን የተፃፈ ነገር ግን ‹ዓሊ አባ ዳማ (የጮሬሣው)› በሚል የብዕር ስም የቀረበ የፈጠራ ታሪክ፤ ተራ ውንጀላ እና የማሸማቀቅ ኢ-ሕገመንግስታዊ ተግባር ተፈጽሞ ሳይም ልቤ ነው የተነካው፡፡ ግለሰቡ ለተቃዋሚ ጥላቻ ቢኖራቸው ላያስገርም ይችል ይሆናል (ትክክል ባይሆንም)፤ ለማንም ፓርቲ ያልወገነ ጋዜጣ ላይ ግን እንዲህ አንደበታቸውን ሲያፍታቱ ግን በእውነት እንደ አገር የሚያሳዝን ነው፡፡

መልዕክቴን ከማጠናቀቄ በፊት ባለፈው ሐሙስ ኅዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም ወሽመጥ ቆራጭ የሆነውን ይህንን የአዘጋጆቹን ከአገር ለቅቆ የመውጣት መርዶ ቀደም ብለን ብንሰማውም ያረግገጥንበትን የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጣቢያን የሶስት አዘጋጆች ቃለ-ምልልስ ላይ ጥቂት ማለት እፈልጋለሁ፡፡ በእውነቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሊደነቁ እና ለመንፈስ፤ ለሞራልም ሆነ ለሞያዊ ጥንካሬያቸው ሊመሰገኑ የሚገባቸው፤ ለአገራቸው የፕሬስ ነፃነት መዳበር ብዙ ሊሰሩ የሚችሉ ወጣቶች ተራ የደህንነት ክትትል እና ማሸማቀቂያ በማድረግ፤ ከዚያም ሲያልፍ በምንጮቻቸው እንደተረዱት የብአዴን ተምክህተኞች መሰብሰቢያ በሆነው በኢቴቪ ስም የማጥፋት ዘመቻ ሊያካሄድባቸው፤ ብሎም በፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ አስደንጋጭ ክስ መስርቶ ሊያሸማቅቃቸው እየሞከረ ስለነበረ አምባገነናዊ መንግስት ሲያወሩ በጣም ነው ያፈርኩት፡፡ ምናልባት ዛሬ አንዳንድ የግል ጋዜጣ አዘጋጆች፤ ‹ምን ቸገረኝ፤ እኔን አልነካኝ› ብለው ዘና ለማለት ይቃጣቸው ይሆናል፤ አንዳንድ ተቃዋሚዎችም ዛሬ ገልበጥ ብለው ቤተመንግስት ኬክ የሚቀርብላቸው፤ ነገም ምናልባት የፓርላማ ወንበር ተሰፍሮ የሚሰጣቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ ተኩራርተው፤ ጋዜጣዋን ገዝተው የሚያነቡም ‹ያሳዝናል ግን ሌላውን አነባለሁ› ብለው ነገሩን አቃልለው ሊተዉት ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ ግን ቂልነት ነው፡፡ ዋ ብያለሁ!!!!! ነግ በኔ ነው፡፡ ‹አዲስ ነገር› ላይ ብትሩን ካነሳ የቅጥረኛ ኤርትራውያን ጥርቅም የሆነው ሕወሓት ነገ ወደ ሌሎቻችን ንጹሀን ዜጎች እንደሚመጣም ከወዲሁ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

በነገራችን ላይ የሪፖርተር ጋዜጣ ባለፈው እሁድ በኅዳር 20 እትሙ ላይ ስለ ጋዜጣው አንድ ሚልዮንኛ ኮፒ መድረስ አስተያየት እንዲሰጡ የጠየቃቸው የኢትዮጵያውያን ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢዴፓ) የዘላለም ሊቀመንበር አምባገነን ልደቱ አያሌው፤ ‹ከድክመት የሚቆጠረው ሌላኛው የሪፖርተር ገጽታ ደግሞ በፊት ገጹ ላይ ‹ፕሬስን ከስቅላት ያድኑ› የሚለው ዓርማና አብሮት ያለው ጽሁፍ ነው፡፡ በእውነቱ ይህ አሁን ፕሬሱ ያለበት ደረጃ ከስቅላት እናድነው የሚያስብል ባለመሆኑ ምናልባት ካስፈለገ ወደፊት ችግሩ ሲመጣ ቦታው ላይ ቢሆን አሁን ግን ብታነሱት የሚል አስተያየት አለኝ› ብለው መናገራቸውን አስነብቦን ነበረ፡፡ እሳቸው ይህን በሚሉበት ወቅት የአንድ የአገሪቱ ትልቅ ጋዜጣ አዘጋጆች ከአገር ውጭ መሆናቸውን እና የጋዜጣው ሌላ ጸሀፊዎችም በስጋት ውስጥ መኖራቸውን፤ ድርጅቱም እንደተዘጋ አጥተውት አልነበረም፡፡ ‹ፕሬስን ከስቅላት እናድነው› የሚለው አባባል አሁን የተጠጉትን እና በስልጣን ላይ ኃይሉን አስተባብሮ እስካለም እንደመኸገር አብረውት የሚጣበቁትን፤ ቀደም ሲል በጥላቻ የወረፉትን መንግስት የሚተችባቸው፤ የሚያሳጣባቸው ማንኛውንም ነገር ማየት ስለማይፈልጉ ነው፡፡ በ 1995 ዓ.ም. እኔ እና እሳቸው በኅዳር ወር በሰሜን ሆቴል የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና ምሁራንን ጋብዘን ‹ለምርጫ 97 የሚረዱ ግንዛቤዎች እና ስጋቶች› በሚል ርዕስ ከፓርቲያችን እና ከአጋሮቻችን ጋራ ጽኁፍ ስናቀርብ ከቀትር በኋላ አቶ ልደቱ ለመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትሩ (በወቅቱ የማስታወቂያ ሚ/ር ነበሩ) ሊደውሉ ወጡ፡፡ ሚ/ሩ ጥሪውን ሳያከብሩ ቀሩ፡፡

አቶ ልደቱም፤

‹አቶ ______________ እንዲህ ብዙ ተቃዋሚ ባለበት እንደሚሸነፉ አውቀው ነው ፈርተው የቀሩት›

አሉ፡፡ ያኔ በአቶ ልደቱ ላይ አልፎ አልፎ፤ አንዳንዴም አላስቆም አላስቀምጥ የሚል የደህንነት ክትትል ይደረግ ነበረ፡፡ ታዲያ ያንን ሁሉ ወከባ ያስረሳቸው ቤተ-መንግስት ገብተው ከኢ/ር ኃይሉ ጋራ የቆረሱት ኬክ ወይንስ የሚቆረጥላቸው ወንበር?

አቶ አህመድ አባጊሣ  አባኡርጌሣ  የተቃዋሚው የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከፍተኛ አደራጅ አባል ናቸው፡፡ ለአስተያየቶቻችሁ ahmedgissa232@gmail.com ን በመጠቀም ሊያገኟቸው ይችላሉ፡፡

www.ethiomedia.com – A site of alternative news and views.
(TPLF is a mercenary-controlled group that cannot be reformed. Like apartheid, it should be dismantled)
December 10, 2009.